ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ሐምሌ 1999 ዓ.ም.

የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች

ቁጥር 11

# መሬትና ስርዓተ- ጾታ በገጠሪቷ ኢትዮጵያ

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

❊❊❊

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

❊❊❊

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

❊❊❊

- በድሬ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

❊❊❊

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## 1. መግቢያ

በሀገራችን ውስጥ ከአለው ህዝብ ውስጥ ግማሽ ያህሉ ሴቶች ናቸው። እነዚህ ሴቶች ከወንዶች በበለጠ በድህነት ተጠቂ ዎች በመሆናቸው የሀገራችን የልማት እንቅስቃሴ ትኩረት ሊሠጣቸው ይገባል። ይህ ትኩረት ሴቶችን በተለይ ተጠቃሚ ለማድረግ ሣይሆን፣ ድህነትን ለመቀነስና ልማትን ለማምጣት አስፈላጊ ነው።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሴቶች በቁጥር ከወንዶች እኩል የሚጠጉ ናቸው። ነገር ግን ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ለድህነት የተ ጋለጡ ናቸው። የመንግስት ፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎች ይህ የተዛባ የሥርዓተፆታ ሁኔታ ለድህነት ቅነሣም ሆነ በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ልማት ትልቅ ችግር መሆኑን በመረዳት ትኩረት እንደሚያሻ ያመለክታሉ።

ለምሣሌ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የሴቶች ፖሊሲ፣ የምግብ ዋስትና እስትራቴጂ እና የድህነት ቅነሣና ልማት እስትራቴጂ ይህንኑ የተዛባ የሥርዓተፆታ ጉዳይ በመጥቀስ ምን መደረግ እንዳለበት ይጠቁማሉ።

የገጠር ሴቶችን የበለጠ ለድህነት ተጋላጭ ነት ከሚያመጡት ምክንያቶች ዋነኛው ሴቶች የተፈጥሮ ሃብቶችን በተለይም የገጠር መሬትን የማግኘት፣ በመ ሬቱ ተጠቃሚ የመሆንና የመቆጣጠር መብቶቻቸው በተግባር የተረጋገጡ አለመሆናቸው ነው። በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የተካሔዱ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመ ለክቱት ሴቶች ከወንዶች ያነሰ መሬት የማግኘት፣ በመሬት የመጠቀምና የመቆጣጠር ሁኔታዎች እንዳሉ ያሣያሉ። የዚህ ፁሑፍ ዋና ዓላማ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ መሬት የማግኘት የመጠቀም የመቆጣጠር ሁኔታዎችን ከሥርዓተፆታ አኳያ ከአሁን በፊት ለማህበራዊ ጥናት መድረክ በቀረቡ ጥናቶች ላይ በመመርኮ ዝ በአጭሩ ማቅረብ ነው።

## 2. የገጠር መሬት ለገጠሩ ነዋሪ ያለው ጠቀሜታ

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖረው ህዝብ ኑሮው በዋነኛነት የተመሠረተው በግብርና ላይ መሆኑ ይታወቃል። ለዚሁ የግብርና ኢኮኖሚ ደግሞ ዋናው መሠረቱ መሬት ነው። የገጠሩ ቤተሰብ መሬት ማግኘት ማለት በዋነኛነት ለኑሮው የሚሆን የምግብ ምርት ማግኘት ማለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ የገጠሩ ቤተሰብ የመሬት ይዞታ ከምግብ ባሻገር የሚያስፈልጉ ወጭዎችን ለመሸፈን እንዲሁም ከመሬት በተጨማሪ አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ግብአት የመሣሠሉ ለምርትና ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችንና አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ወሣኝ ሚና ይጫወታል። የመስክ ጥናቶች እንደሚያሣዩት በቂና ለም መሬት ያላቸው አባወራዎች የተሻለ የምግብ ሰብል ከማምረታቸውም በተጨማሪ ብድር እንዲያገኙ፣ ማዳበሪያና ሌሎች ግብአቶች እንዲያገኙ፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። እነዚህ ሁኔታዎች ሲታዩ የገጠር ድህነትና ልማት በዋነኛነት ከመሬት ይዞታ ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን ያሣያሉ።

## 3. በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬት የሚያገኙባቸው መንገዶች

እንደሚታወቀው የ 1967 ዓ.ም የገጠር መሬት አዋጅ የመሬት ባለቤትነትን ሙሉ ለሙሉ ወደ መንግስት ከማዛወሩ በተጨማሪ መሬት መሸጥና መለወጥን ይከለክላል:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በተለይ በአርሶ አደሩ አካባቢዎች የገጠሩ ህዝብ መሬት የሚያገኝባቸው ዋና ዋና መንገዶች የሚከተሉት ናቸው::

### 3.1. ከቤተሰብ በውርስና በስጦታ

በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል መሬትን ከቤተሰብ በውርስና በስጦታ ማግኘት የተለመደ ጉዳይ ነው:: የመስክ ጥናቶች እንደሚሳዩት በአርሶ አደሩ አካባቢዎች ውርስና ስጦታ ዋነኛ መሬት የማግኘት መንገዶች ሁነው ይገኛሉ:: በዚህ መንገድ ተወላጅ ልጆች ወይም ጧሪና አገልጋይ ሁነው የቆዩ ግለሰቦች ከወላጆች ወይም ከተጧሪ አባወራዎችና እማወራዎች መሬት ያገኛሉ::

### 3.2. በመሬት ክፍፍል

እንደሚታወቀው ከ 1967 የገጠር የመሬት ይዞታ ለውጥ በኋላ የቀበሌ ገበሬ ማህበራት በየጊዜው ከቀበሌያቸው ውስጥ የመሬት ክፍፍል በማድረግ መሬት ለሌለው እና ላነሰው መሬት ሲሰጡ ቆይተዋል:: በእርግጥ ይህ መሬትን የማከፋፈል ሁኔታ በሀገሪቱ በሞላ በመመሪያና በወጥነት ይካሄድ የነበረ ሳይሆን በየአካባቢው በተለያየ መንገድ ተግባራዊ ሲሆን የቆየ ነው:: በዚህም የተነሳ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በጣም ብዙ ጊዜ ክፍፍል የተደረገባቸው ቦታዎች ሲኖሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ከ 1967 የይዞታ ለውጥ በኋላ ምንም አይነት የመሬት ክፍፍል አልተካሄደም:: ከደርግ መንግስት መጨረሻ አመት ጀምሮ ይህ አስተዳደራዊ የመሬት ክፍፍል የይዞታ ዋስትናን ያሳጣል በሚል ዋነኛ ምክንያት እየቀረ የመጣ ቢሆንም ከደርግ በኋላም በአንዳንድ አካባቢ ዎች ተግባራዊ የተደረገና አሁንም በመሬት አስተዳደር ህጎች ውስጥ የሚገኝ ነው::

### 3.3. በመሬት ግብይት አማካኝነት

የመሬት ግብይት መሬት በጥማድ፣ በኪራይ፣ በለውጥ፣ በወለድ አገድ፣ በሽያጭና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ከአንድ ግለሰብ/ቤተሰብ ወደሌላ የሚተላለፍባቸውን ሁኔታዎች ያካትታል::

የ 1967 ዓ.ም የገጠር መሬት አዋጅ አብዛኛዎችን የመሬት ግብይት አይነቶች የከለከለ ቢሆንም የመስክ ጥናቶች እንደሚያሣዩት በተለይ የመሬት ጥማድና ኪራይ በሠፊው ሲሰራባቸው የቆዩና ያሉ ናቸው:: አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሣዩት በጥናቶች ከታዩት ከጠቅላላ ማሳዎች ወደ አርባ ከመቶ የሚጠጉ ማሣዎችና ከጠቅላላ አርሶ አደሮቹም ከዚህ መጠን በለጥ ያሉ አርሶ አደር ቤተሰቦች በመሬት ግብይት ውስጥ የተካተቱ ናቸው::

### 3.4. በሌላ አካባቢ በመስፈር

በደርግ ጊዜም ሆነ ከደርግ በኋላ መንግስት የገጠር ድህነትን ለመቀነስ በተለይም ደግሞ የመሬት ጥበትንና በተፈጥሮ አደጋ የሚመጡ ችግሮችን ለመከላከልና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከሚከተላቸው ስልቶች አንዱ የሠፈራ ፕሮግራም ነው:: በአሁኑ ጊዜም በመንግስት እይታ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሰፊ ለምና በማንም ያልተያዙ መሬቶች በብዛት ስላሉ በተለይ ከደጋማው አካባቢ ለምነቱን ካጣው፣በድርቅ ከሚጎዳውና መሬት ከጠበበበት አካባቢ የሚኖሩ አርሶ አደሮችን ወደ ለም ቦታዎች ማዛወር የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የገጠር ልማትን ለማሻሻል ጠቃሚ እርምጃ ተደርጎ ተወስ ዷል:: ስለሆነም የሠፈራ ፕሮግራም በተለያዩ ጊዜያት በመንግስት እየተነደፈ ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል:: ሠፋሪ ዎች በአዲሱ የሠፈራ አካባቢ በቂና ለም መሬት እንደሚያገኙም ይጠበቃል:: ሆኖም ባጠቃላይ ሲታይ ግን የገጠሩ ህብረተሰብ መሬት የማግኘት ዕድሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠበበ፣ መሬት የሌላቸው የገጠር ነዋሪዎች ቁጥርም እየጨመረ ይገኛል::

## 4. የገጠር ሴቶች ሁኔታ

የተለያዩ የመስክ ጥናቶች የሚያመለክቱት ሴቶች በተለይ ደግሞ በእማወራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ከወንዶችና በአባወራ ከሚተዳደሩ ቤተሰቦች ያነሰ መሬት እንደ ሚያገ ኙ፣ በመሬቱም የመጠቀም ዕድላቸው ከወንዶች ያነሰ እንደሆነ ነው:: ለዚሁ ምክንያት ናቸው ተብለው የሚጠቀሱ ብዙ ሁኔታዎች አሉ:: ለምሳሌ በሃገራችን ሰፍኖ የሚገኘው አባታዊ (ፓርሪያርካል) ስርዓት የወንድን የበላይነትና የሴትን የበታችነት የሚያስፋፋ በመሆኑ በሃብት፣ በፖለቲካ፣ በአገልግሎት ማግኘትም ሆነ በሌላ መስኮች ሴቶች በበታችነት እንዲገኙ አድርጓል:: ለምሣሌም የቤተሰብ ሃላፊ ባል ነው፣ ሴት ትዳር ስትይዝ ወደ ባሏ መኖሪያ ቦታ ትሔዳለች፣ ወንድ አደባባይ ሴት በቤት ይውላሉ ወዘተ:: በነዚሁ ምክንያት የሴቶች መሬት የመውረስም ሆነ የመቆጣጠር መብት ከወንዶች ያነሰ ነው::

ሌላው ያታዊ የስራ ክፍፍሉ ሴቶችን ለቤት ሥራ ወንዶችን ለአደባባይ በማድረጉም በተጨማሪ በግብርናም እረገድ የዕርሻ ሥራ (በሬ ጠምዶ የማረስ) የወንዶች በመሆኑ ገበሬ በዋነኛነት ወንድ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ በዚህ አይነት ፓትሪያርካዊ ሥርዓት ውስጥ የገጠር ሴቶች መሬት የማግኘትም ሆነ በመሬት የመጠቀም እድላቸው ከወንዶች ያነሰ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን የገጠር የዕርሻ መሬት የሚገኙባቸው መንገዶችን ስንመረምር ሴቶች ያሉበትን ሁኔታ ያሣዩናል፡፡

ውርስና ስጦታ ዋነኛ የመሬት ማግኛ መንገዶች እንደሆኑ ቢታወቅም በባህል ደረጃ ሴት ልጅ በጋብቻ ጊዜ ወደ ባሏ የመኖሪያ አካባቢ ስለምትሔድ ከወላጆች መሬት የማግ ኘት ዕድሏ ጠባብ ነው፡፡ ስለዚህ በዋነኛነት ባሏ ከወላጆች ወይም ከሌላ ምንጭ ያገኘውን መሬት በመጠቀም ትኖራለች፡፡ ይህ ሁኔታ ባሏ ሲሞትም ሆነ በፍች ሲለያዩ ሴቷ አካባቢውን ለቃ እንድትሔድና መሬትም እንድታጣ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በፖሊሲ ረገድም ቢሆን ከደርግ ጊዜ አንስቶ አሁንም መሬት የሚሠጠው በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ ለሆነ አርሶ አደር ብቻ በመሆኑ ቀበሌውን ለቅቆ የሚሔድ ወይም ከሌላ ቀበሌ የሚመጣ ሠው መሬት የማግኘት እድሉ በጣም የጠበበ ነው፡፡ ስለዚህ በፍች ወይም በባለቤቷ ሞት ምክንያት አካባቢውን ለቃ የምትሔድ ሴት መሬቷን ታጣለች ማለት ነው፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአካባቢ አስተዳደሮች (በቀበሌ) የሚደረጉ የመሬት ክፍፍሎችም ሴቶችን ብዙ ተጠቃሚ አላደረጉም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መሬት የሚሠጠው በቀበሌው በቋሚነት ለሚኖር አርሶ አደር በመሆኑ ሴቶች አካባቢያቸውን ይለቃሉ ወይም በባህሉ መሰረት አምራች ገበሬዎች አይደሉም ተብሎ ስለሚታሰብ በመሬት ክፍፍል ውስጥ ከወንዶቹ እኩል አይታዩም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ጊዜ የአካባቢ ባለስልጣናት በጉቦና በአድሎ ስለሚሰሩ ሴቶች በክፍፍሉ ወቅት መሬት የማግኘት እድላቸው የጠበበ እንደሆነ አንዳንድ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

ለምሳሌ ሚስት የሞተችበት አባወራ መሬቱ ሙሉ ለሙሉ ሲከበርለት ባሏ የሞተባት እማወራ ግን ከቤተሰቡ መሬት ተቀንሶ ለሌላ እንደሚሰጥ ጥናቶች ይጠቅሳሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በተለይ በጋብቻ ሲቆዩ ልጅ ባልወለዱ ሴቶች የከፋ ነው፡፡ ለዚህ አንደኛው ምክንያት ሚስቱ የሞተችበት አባወራ እዚያው ቦታ በመኖር ሚስት እንደሚያገባና ልጆቹንም እንደሚያሳድግ ሲጠበቅ ባሏ የሞተባት እማወራ ግን ወይ አካባቢውን ለቃ እንደምትሄድ አልያም በአካባቢው ባል እንደማታገባ ስለሚቆጠር ነው፡፡

የመሬት ግብይት ስርአት እንደዚሁ ደሃዎችን በተለይ ደግሞ ሴቶችን ብዙ ተጠቃሚ እንደማያደርግም ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የመስክ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ መሬቱን የሚያስጠምድ እና የሚያከራይ ጉልበት፣ በሬና ሌላም አስፈላጊ የግብርና ግብአቶች የሌሉት ሰው ነው፡፡ ስለዚህ ሴቶች ወይም እማወራዎች የወንድ ጉልበት፣ በሬና ሌሎችም ግብአቶች በአብዛኛው ስለሌሉዋቸው መሬታቸውን ለማስጠመድ ወይም ለማከራየት ይገደዳሉ፡፡ መሬት የሚጠመዱት ወይም የሚከራዩት ደግሞ የተሻለ ጉልበት፣ በሬና ሌሎችም ግብአቶችም ያሏቸው ሲሆኑ እነዚህ ደግሞ በዋነኛነት ወንዶች ወይም አባወራዎች ናቸው፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በጥማዶ ወይም በኪራይ የተ ሰጠው መሬት ሲታረስ ከባለመሬቱ የሚጠበቁ ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ መሬት በጥማዶ ሲታረስ ባለመሬቱና ተጠማጁ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ጉልበትእና የመሳሰሉትን ወጪዎች የሚጋሩበት ሁኔታ አለ፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ለማሟላት ሴቶችና እማወራ ዎች በድህነት የተነሳም ሆነ በሌላ ምክንያት እንደሚቸገሩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሴቶች መሬታቸውን ለማስጠመድ እና ለማከራየት በጣም ይቸገራሉ አልያም በዝቅተኛ ድርሻ ወይም ኪራይ መሬታቸውን ይሰጣሉ ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም በጥማዶ የሚሰጥ መሬት በአግባቡ ለመታረሱ እና ለሰብሉ አስፈላጊውን እንክብካቤ ለመደረጉ ክትትልና ቁጥጥር የሚያስፈልግ ሲሆን የመስክ ጥናቶች እንደሚሳዩት ሴቶች ይህንን ማድረግ ባለመቻላቸው ያስጠመዱት መሬት በወቅቱ እንደማይታ ረስ፣ እንደማይታረም እና ሌሎችም ተገቢ እንክብካቤዎች እንደማይደረጉለት ነው፡፡ ይህም ሁኔታ ሴቶች በተገቢው ሁኔታ የመሬታቸው ተጠቃሚዎች እንዳልሆኑ ያሳያል፡፡

በአሁኑ ጊዜ መሬትን በተመለከተ እየተካሄደ ያለው የመሬት መመዝገብና የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት እንቅስቃሴ የሴቶችን የመሬት ይዞታ እና የመጠቀም መብቶች እንደሚያጠናክር ቢጠበቅም ጥቂት ጥናቶች እንደሚጠቁሙት የመሬትን ይዞታ ከማረጋገጥ አኳያ ችግሮች መኖራቸውን ነው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ቦታ «በመሬት» አስተዳደር ኮሚቴዎች ውስጥ ያለው የሴቶች ተሳትፎም አናሳ መሆኑንም ይጠቅሳሉ፡፡

## 5. ማጠቃለያና የፖሊሲ ጥቆማዎች

ከቅርብ አመታት ወዲህ በመንግሥት የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ የሚያግዙ የተለያዩ እርምጃዎች እየተወሰዱ መሆኑ ይታወቃል:: ሴቶች ከወንዶች እኩል የሆኑ የንብረት መብቶች እንዳሏቸውም ከህገ መንግስት ጀምሮ በሌሎች ህጎችና ፖሊሲዎች ተቀምጠዋል:: ሆኖም በተለይ የገጠር ሴቶችን በተመለከተ የንብረት መብቶቻቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ገና ብዙ እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው የገጠር መሬትና ሥርዓተ ፆታን በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች ያሣያሉ::

በህግና በፖሊሲ ደረጃ ለሴቶች የተሰጡ መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብቶች ተግባራዊ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ ብዙ መሠናክሎች አሉ:: አንዳንድ ጊዜ ሴቶች ከወንዶች እኩል የንብረት መብት እንዲኖራቸው የሚደነግጉ የተሟሉ ህጎች የሉም:: ለምሣሌ በግለሰብ የቤተሰብ ሃላፊ ስም እንዲመዘገቡ የሚደረጉ የንብረት መብቶች በወንድ ወይም በባል ስም የሚመዘገቡ መሆኑ ይታወቃል:: ሌላ ደግሞ መሬት የማግኘትን መብት በተወሰነ ቀበሌ ውስጥ ከመኖር ጋር የሚያቆራኙ ህጎች አሁንም አሉ:: በአገሪቱ በሠፈነው ፓትሪያርካዊ ስርዓት የተነሣ በፍች ወይም በባል ሞት የቆዩበትን አካባቢ የሚለቁ ሴቶች የመሬት መብታቸው እንዴት ተጠብቆ እንደሚቆይ በግልፅ መደንገግ ይገባዋል:: ከዚህም በተጨማሪ በመሬት የመጠቀም መብት በተግባር የሌሎች ሀብቶችና ግብአቶች ባለቤትነትን ይጠይቃል:: ለምሣሌ የጉልበት፣ የበሬ፣ የገንዘብ (ብድር):: ስለሆነም የሴቶችን መሬት የማግኘት መብት ከመደንገግ ባለፈ ሴቶች በመሬቶቻቸው ተጠቃሚ የሚሆኑባቸውን ተጨማሪ እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል::

የሴቶችን መብት ከማስከበር አኳያም በአገሪቱ ያለውን ፓትሪያርካዊ ስርዓት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ እገዛዎች የሚደረጉበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል:: ለምሣሌም ሴቶች መብታቸውን እንዲያውቁና እንዲያስከብሩ የህግ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል::

ሴቶችን የመብቶቻቸው ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ከፖለቲካ ባሻገር ተግባራዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው የሴቶች ጉዳይን የሚከታተሉ መንግስታዊና የአካባቢ የሴቶች ተቋማት ያስፈልጋሉ:: ለምሣሌ የገጠር ሴቶች ተደራጅተውና ከመንግስትና ከሌሎች አካላት በሚደረግላቸው ድጋፍ የንብረት መብቶቻቸውን ሊያስከብሩና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞችን ሊያገኙ የሚችሉባቸውን ሁኔታ ማሻሻል ይቻላል::

ሌላው ጠቃሚ እርምጃ መንግስት በሚያወጣቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎች ውስጥ ሥርዓተ ፆታን ማካተት ነው:: ለምሣሌ የመሬት ህጎችና ፖሊሲዎች ሥርዓተፆታን አካተው መውጣት ይገባቸዋል:: ይህ ማለት ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው ብሎ መደንገግ ብቻ ሣይሆን ያለው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ሴቶችን በምን ሁኔታ ያስተናግዳል ብሎ በመመርመር፣ለሴቶች እኩልነት አመች ያልሆኑ ሁኔታዎችን በሚለውጥ መልኩ ህጎችን ፖሊሲዎችንና እስትራቴጂዎችን መቅረፅ ነው::

ለማጠቃለል፣በሀገራችን ልማትን ለማምጣትና ከድህነት ለመውጣት በሚደረገው ትግል ለድህነት በበለጠ ተጠቂ የሆኑ ሴቶችን ጉዳይ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው:: በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በድህነት ውስጥ ያሉ ሴቶችን ከድህነት ለማላቀቅ መሬት የሚያገኙበትንና ከመሬት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታዎች ፖሊሲ በማውጣትም ሆነ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ በማድረግ ሒደት ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል::

**ይግረመው አዳል**

**ምንጭ:-** Yigremew Adal. FSS. 2001. Land Redistribution and Female –Headed Households: A Study in Two Rural Communities in North West Ethiopia. FSS Discussion Paper No. 5. Addis Ababa: FSS.

Yigremew Adal. 2006. Rural Women’s Access to Land in Ethiopia. In *Land and the Challenges of Sustainable Development in Ethiopia*, edited by Dessalegn Rahmato and Taye Assefa. Addis Ababa: FSS.

**Acknowledgement & Disclaimer**

*This document has been produced with the financial assistance of the European Union. The contents of this document are the sole responsibility of the author and can under no circumstances be regarded as reflecting the position of the European Union.*

አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: 011-157 29 90/91 ♦ ፋክስ: 011-157 29 79
ኢ.ሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et